# *ሱሴ*

**“Nothing is sweeter and addictive than power, the unlucky soul this demon possesses, if he is not sacrificed on its altar will sacrifice others himself to get it”**
**— Bangambiki Habyarimana, Pearls Of Eternity**

*“እንደ ሥልጣን ጣፍጭና ሱስ ምንም ነገር የለም፤ ይህ ርኩስ መንፈስ የተላብስ ሱስና ጣፋጭነት ለመስዋት ካልተቻለ ራሱን ለማኖር ሌሎችን ከመስዋት ወድ ኃላ አይልም፤” ባንጋሚቢኪ ሓሪማና፣*

*ዘመን አልፎ ዘመን በተተካ ሰዎች እንዲህ አደርጋሎሀ ይህን እፍጽማሎሀ የሚል የምኞት ቃላትን ምሰንዘርና መጠጥን፤ ሲጃራን አቆማሎሀ የሚሉ የተስፋ ቃላት መስማት የተለመደ ነው፤ ከነዚህ የተስፋና የምኞት አባባሎች በስተጀርባ በወስጠ ታዋቂነት በጎና ጎጂ ስንክሳሮች አሉ፤ በተለይ በሱስ የሚፈረጁ ጉዳዮች ሁሉ ሁለት ገጽታ አላቸው፤ ለምሳሌ መጠጥና ሲጃራ ማቆውም ይቻላል ቢባለምና ጥቂቶች ከሱስ ቢገላገሉም፤ በሚልዮን የሚቆጠር ሕዝብ ለሕልፈተ ህይወት እየዳረገ ይገኛል፤ ከዚህ ሁሉ በላይ ግን እስከ ከርሰ መቃብር ራሱን ብሎም ሱሴን ያደንቅፈኛል የሚለውን ኃይል የመሸኘት አቅም ያለው ትልቁ ሱስ ሥልጣን ነው፤*

*በተለያየ መንገድ ማንም ይሁን ማንም አንዴ ሥልጣን ላይ ከወጣ ርስተ ጉልት ይመስል የሙጥኝ ብሎ ሕግንና ስብዓዊ መብትን በመደፍጠጥ እንደ የሊብያው ጋዳፊ፤ እንድ የኢራቁ ሳዳም በአስፋሪ ሁኔታ ሕይውትን ማጣት አልያም የሌላውን ሕይወት በማጥፋት በርካቤ ስልጣን መኖርን ይመርጣሉ፤ ለዚህ ነው ሓሪማና እንድ ሥልጣን ጣፋጭና አስቀያሚ ሱስ የለም ያሉት፤*

*በሀገራችንም በተለያይ የታሪክ አጋጣሚ ወደ ሥልጣን የወጡት ከአጼ ኃይለስላሴ ጀምሮ በተለያይ ዜዴ በሥልጣን ለመቆየት የተደረጉ ጥረቶች ከዚሁ መሪር ሱሰኝነት የመነጨ ነው፤ ያለፉትን መንግሥታት ወደጎን አድርገን ያለንበትን ስንፈትሽ የዚህ የሥልጣን ሱሰኝንት ምንነት በግልጽ ያሳየናል፤ ሕዋሓት መር ኢሓዲግ በሥልጣን ለማቆየት ሕዋሓት መር ቡድን ያዙኝ ልቀቁኝ እያለ ያለው ከዚህ የመነጨ ነው፤*

*የሕዋህት ቱባ ባለስልጣናት ለ27 ዓመታት ለአንድ ቀን አዳር እንካ ያልተመኙትን ከተማ ሙጥኝ ማለቱ ሕገ መንግስት ተጣሰ ብሎ መፈክር ማስማቱና ተመርጦና መርጠው በፌደራል ፖሊስ የሚጠበቅ መኖርያቸውን ጥለው መቀሌ ውስጥ በየሆቴሉ መመሸግ ከዚሁ የሥልጣን ሱስ ለመመንጨቱ ፈንትው ያለ ሀቅ ነው፤*

*እዚህ ላይ ሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ይህን የማያሻማ ዑነታ ሊረዳ ይገበዋል፤ የትግራይ ሕዝብን ብቻ ሳይሆን በህዋሃት ውስጥም በቅን ልቦና የወጣትነት ዕድሜያቸውን ሰውተው በቆንጮዎች ሴራ ተጠልፈው ወይም ወደውና አምነውበት የታገሉ የኃላ ኃላ ያልተመቹ አልያም ለምን በለው የጠየቁ እንዲሁም በብቃትም በቁርጠኝነትም ከነሱ የተሻሉ በስብአስባብ የተወገዱ፤ አማራጭ አጥተውም አንጀታቸው እየተቃጠል አብረው የተጋዙም በማነኛውም መስፈርት ከሕዋሃት ነጥሎ መመልከትና እንደማነኛውም አትዮጵያዊ የዚህን የለውጥ ማዕበል ተጠቃሚ እንዲሆን መረባርብ የግድ ይለናል፤_በርግጥ በየአካባብው የጥቅምና የዝምድና ሓረግ ያላቸው ትግርኛ ተናጋሪ ጥቂት ስዎች የሚያደርጉት ድርጊትና ዕነቅስቅሴ የተራው የትግራይ ሕዝብ የማይወክል መሆኑ ልንረዳ ይገባል፤ ይህን አለመገንዘብ ደግሞ ሕዋሃት ላጠመደው ወጥመድ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው፤*

*የተለየ ሀሳብ ነውር በሆነበትና የውሸት ፕሮፖጋንዳ ቀን ከሌሊት በሚለፈፍበት የግንብ አጥር ያለን ሕዝብ ሁኔታ ለመረዳት ህዋሀት መር ኢሃዲግ መላ ሀገሪቱ ሲመራ በነበረብት የዛሬ 6 እና ሰባት ወራት በፊት እንዴት እንደነበር መለስ ብሎ መቃኘት ያስፈልጋል፤  ያሁኔታ ውስጥ ያለፈ በቻ ሳይሆን የስማ ያየ የትግራይ ሕዝብ አሁን ያለበትን ሁኔታ ይረደዋል የሚል ዕምንት አለኝ፤*

“The politicians of your country will always try to encircle you with the high walls of lies! You must know that the truth is beyond the walls and without meeting the truth you cannot meet the freedom!”
**— Mehmet Murat ildan**

***“የአገራቹሁ ፖለቲከኞች ሁሌም በሰማይ ጠቅሰ የውሸት ግንብ ሊከባቹሁ ይሞክራሉ፤ ይሁንና ዑነቱ ግን ያለው ከግንቡ ወዲያ ማዶ ነው፤ ስለሆነም ዑነቱ እስካላገኞቹህ ነጻ አይደላቹሁም” መህምት ሙራት ኢልዳን***

የትግራይ ሕዝብም መህመት ሙራት እንዳሉት ዑነቱ ያለው ከተገንባላቹህ የውሸት ግንብ ወዲ ማዶ መሆኑ ተገንዝባቹህ መተኪያ በሌለው የልጆቻቹሁ ሕይወትና በጉልበታቹሁ በንብረታቹህ የከፈላቹሁት መስዋዕትነት በጥቂት የአንድ መንደርና ቤተሰብ ስብስብ ሳትወናበዱ ኢትዮጵያዊነታቹሁ ጀግንነታቹሁ ዛሬም እንደቀድሞው ልታስመስከሩ ይገባል።

የትግራዋይ ኢትዮጵያዊነት ለጥያቄ የሚቀርብ ጉዳይ አይደልም፤ ለትግራዋይ እንደማነኛውም ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊነት የመኖርና ያለመኖር ጉዳይ እንጂ ሲፈልገ የሚለበስው ሳይፈልገው የሚያወልቀው ተራ ካባ አይደለም፤ ደሙ ትንፋሹ ማለት ነው፤ በመሆኑም ከኢትዮጵያ ፍላጎት ውጭ ፍላጎት የለውም፤

ዛሬ ጽዋው ሞልታል ከዚህ በላይ መስፈር ጉዳት እንጂ ጥቅም የለውም ውሸት ከውሸትነቱ አያልፍም የኢትዮጵያ ሕዝብ የይቅርታ ሕዝብ ነው፤ መሳሳት ያለነው በስህተት ስህተት መጨምርና ሌላውን ማሳሳት ግን ለይቅርታ ልብም ዕንቅፋት ነው፤ በተለየ የበሰለ ፖለቲከኛ በአንድ ወቅት የሰራ ስትራተጂ ሁሌም እንደማይሰራ ይረዳል፤ በሽምቅ ውጊያ ጊዜ የጠቀሙ መላምቶች ሴራዎች እንደ መንግስት አይሰሩም ብሎ ያምናል ማመንም አለበት፤

የትግራይ ሕዝብ ለከፈለው መስውዕትነት  ለተመኘው ፍትህን የግለስብ ነጻንትና ኑሮን ልጆችን ገብሮ ኑሮውን አምሳቅሎ በሌላ ሳይሆን ለድል እንዲበቁ በረዳቸው ስዎች ለ27 ዓመት እንዳቋመጠ ምኞቱ መና አስቀርተውብታል።

ምንም እንኳ ኢንደውመንት ደርግ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በጎ አድራጎት ሲያፈርስና እንደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ፋብሪካ፤ ሞዝቦልድና ተያያዥ ተቋማትን ሲወርስ ሕጉ የተሻረ ቢሆንም ህዋሃት ህጉን መልሶ ወደነበርበት ለመመለስም ሕግና ሕግ በሚፈቅድው ለመጓዝ ሳያስፍለገው በትግራይ ሕዝብ ስም በክልሉ የተቋቋሙ ተቋማት ለትግራይ ሕዝብ ላማ አልቸኝ በሰማይ ወተትዋንም አላይ እንዲሉ ስም እንጂ የፈየደው ነገር የለም። ይልቁንስ ለቱባዎቹ የሕዋሃት መሪዎችና ቤተስቦች የማትነጥፍ ጥገት ሆነው ሲያገልገሉ ኑረዋል።አሁን ደግሞ የሌለ ስንክሳር በማነብነብ እምቦቅላ ወጣታቶችን በጸጥታ ኃይል ስም በማባባልና የወራት ሥልጠና ሰጥቶ ዩኒፎርም በማልበስ በከተማና በገጠር እንዲግንጎራደዱ በማድረግ ከህዝብ ጋር ለማላተምና በህዝቡ ላይ የስነ ልቦና ጫና ለማሳደር ሲወራጩ በሌላ በኩል በገንዘብ ህሊናቸው በናውዘ ስዎች በሬ ወለደ ተረት ተረት ህዝቡን ውዥንብር ውስጥ እይከተቱት ይገኛሉ

Political language. . . is designed to make lies sound truthful and murder respectable, and to give an appearance of solidity to pure wind. George Orwell

“የፖለቲካ ቋንቋ ______ የተቀመረው ውሸትን እንድ ዑነት እንዲስተጋባ፤ ግድያን የተቀደሰ ምግባር ለማስመሰልና የውሸቱ ንፋስን ጠጣር እንጎቻ አስምስሎ ለማቅረብ ነው፤” ጆርጅ ኦርዊል

ጆርጅ ኦርዊል አኒማል ፋርም በሚለው ጽሁፉ እንዳለው የፖለቲካ ቋንቋ በሚያማለል የቃላት ስብስብ ዛሬም የተለመደው ቅጥፈትና ውሸት በማናፈስ ያኑኑ የትግራይ ሕዝብ (በላኤ ሰብ) ስው በላ መጣብህ በሚል እንጉርጉሮ ውዥንብር ውስጥ ከተውታል፤ የሚገርመው ትግራይ ውስጥ ሙህር እንዴሌለ የመንድራቸው ስዎችና የጥቅም  ተካፋዮች ሙሁር እየተባሉ የሚቀርቡት በውል ስም ሰዎች ማላዘን ዑነትን ማጣመምና የህዋሃት አመራሮች የሚሉትን ማስተጋባት ትዕዝብት ይጫራል፤ ለትግራይ ሙህራንም ስድብ ነው።

በዘመናዊ ፖለቲካ ማሸነፍና መሸንፍ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ነው፤ አሁን የምናወራው ፖለቲካ ከቀደሞቹ የፖለቲካ ስርዓቶች የሚለየውም ይህው ነው፤ ትናንት ስለዲሞክራሴ ያወረሉን ይህን  ሀቅ መቀበል ያቃታቸው ይመስላል፤ ይህ ብቻ ግን አይደለም ያንኑ ለስልጣን ያበቃቸው የፖለቲካ ቋንቋ ዛሬም ሊጠቀሙ መዳዳታቸው ነው፤ በርግጥ የሥልጣን ሱስ ምንነት የሚያሳይ ከመሆኑ ሌላ ሊሆን አይችልም፤ ወደ ሥልጣን ሲወጡ ያሉቱን ዲሞክራሲም እየደፈጠጡ መሆኑ የተገነዘቡ አይመስልም፤

በርግጥ ሌሎችን አግሎ በመንደር፤ በዝምድና በአምቻ ጋብቻ የተዋቀረ ድርጅት አሁን ከሚያሳየው ባሕሪና ድርጊት ውጭ መጠበቅ ሞኝነት ቢምስልም ዓይን ያፈጠጠ ዕንቅስቃሴው የማን አልበኝነት፤ መህይምነትና ትዕቢት ነጸብርቅ ለመሆኑ ምስክር መቁጠር አይስፈልገውም፤ እንዲያውም በዛሬዎቹ የለውጥ አራማጆች ይደረግ የነበረው ሕቡዕ ዕንቅስቃሴ አንዳንድ ቱባ ባለሥልጣኖች ሲያነሱ ተዋቸው የትም አይድርሱም የሚል ምላሽ ክዋናዎቹ የድህንነት፤ የወታደራዊና የፖለቲካ መሪዎች ይስጥ እንደነበር ለአምራሩ ቀሬቤታ የነበራቸው ስዎች በቁጭት እንደሚያወሩ በስፊው ይናፈሳል፤ ይህም የሚያሳየው ትዕቢቱና ንቀቱ የትና ሌላ ደርሶ እንደነበር ማሳያ ብቻ ሳይሆን ጽዋው ሲሞላ ምንም ይሁን ምንም ሊገታውና ሊያቆመው እንደማይችል ነው፤

በአንዳንድ ሰዎች ላይ እየተወሰደ ባለው ዕርምጃ ብዙ ውዥንብር ቢፈጥርም እየሆነ ያለው መሆን ያለበት ነው፤ በሃገራችን አባባል ዓሳ የሚገማው ከጭንቃላቱ ነው እንደሚባለው ከቁንጫው መጀምሩ ትክክል ቢሆንም አንዳንድ የግልና የቡድን ፍላጎት ለማራመድና የሚሹ ጊዜ ለመግዛት ትርጉሙን በማዛባት በአንድ ብሄረስብ ያነጣጠረ አድርገው ያቀርቡታል፤ ዑነቱ ግን የአደባባይ ሚስጥር ነው፤ ከ1983 የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ጀምሮ በቁንጮው የሥልጣን ዕርከን የተቀመጡት በአብዛኙው የወጡት ከአንድ ቤሄር በመሆኑ እንጂ ሆን ተብሎ አለመሆኑ የሚካድ ሀቅ አይደለም፤ ይህም ሲባል ከሌላ ቢሄር የወጡ ሁሉ ከደሙ ንጹህ ናቸው ማለት አይደለም፤ ይሁንና ሀገሪቱ ካላት አንገብጋቢ አጀንዳዎች፤ የፍትህ አከላት የሰው ኃይልና የኢኮኖሚ አቅም በየደረጃው እንጂ ሁሉንም ነቅሼ በአንዴ ልቅረፍ ብትል ጫናው ቀላል አይሆንም፤ እንዲያውም አንዱ ሀያሲ እንዳሉት እንዲህ ዓይነት የጅምላ አካሄድ ቢውጠን ማጎርያውም ይቸገራል፤ሌላውንም አጀንዳ ያዘናጋል ያኮሰምናልም።

እንዲህና እንዲህ እየተባለ ነገሮች ሳይታሰብ ከቁጥጥር ውጭ ይሆኑና ወደአላስፈላጊ መንገድ በመሄድ ምንም የማያቀው የዋህ ሕዝብ የማይገባ ወስዋዕትና ዕዳ ከፋይ ይሆናል፤ ሁሉም የተነገረውን በጥሬው ሳያኝክና  ሳያላምጥ ይውጥና ማዋሀድ ሲያቅተው የስቃይና ያላስፈላጊ መስዋዕትነት ለመክፈል ይገደዳል፤ ሂትለርና ጋደኞቹ የጀርመንን ሕዝብ ከኃላቸው ለማሳለፍ የተጠቀሙት ዜዴ ፖአንዳውያን ጀርመኖችን ገደሉ አሳደዱ የሚል የአዞ ዕንባ በማንባት የጀርመናውያን ቢሄርተኘት ማራገብ ነበር፤የተመኙት አልቀረም ቢሄርተኝነቱን ቆስቁሰው ፖላንድን በመወረር የናዚ አጀንዳቸውን ማራመድ ጀመሩ፤ ዓለም አይቶት የማያቀው ዕልቂትና መፈናቀል ደረሰ፤ እስከ ዛሬም ድረስ ጠባሳው አልጠገገም፤

 “understand that all battles are waged on an unconscious level before they are begun on the conscious one, and this battle is no different. The power structure wishes us to believe that the only options available are those which they present to us, we know this is simply not true, and therefore we must redefine the terrain of this conflict, and clearly, it is a conflict of worldviews and agendas." - Teresa Stover

“መረዳት ያለብን ሁሉም ጦርነተቾ ታስበቦት ሳይሆን ሲንሱ ባልታሰበ ሁኔታ ነው፤ የትኛውም ጦርነት ልዩ ባህሪ የለውም፤ በሥልጣን ያለው መዋቅር ከዚህ የተለየ አማራጭ እንደሌለ እንድናምን ይሻሉ፤ መንም እንኳ ይህ ውሸት መሆኑ ብናውቅም፤ ይሁንና የዚህን ጦርነትና ግጭት ምንነት ደጋግመን ስንፈትሸው ፍንትው ብሎ የሚታየው የዓለማና የአመለካከት ልዩነትና አጀንዳ ሆኖ እንገኘው አለን፤ ቴሬሳ ስቶቮር

ቴሬሳ ስቶቮር እንዳሉቱም ሂትለር ሌላ አቋራጭ እንድሌለው የጀርመን ሕዝብ ለማሳመን በጉብላ በሚመራው የፕሮፓጋንዳ መዘውሩ ያልፈነቀለው ዲይንጋይ አልነበረም፤ የኃላ ኃላ ግን ለጀርመን ልዓለም ሕዝብ የተረፈው ሐፍረትና መሸማቀቅ ውርደትና ዕልቂት ህሊና ሊሸከመው ከሚችለው በላይ ነው፤ ዛሬ በሀገራችን እያይን ያለው ተመሳሳይ አንጃ ግራንጃ ምንም እንካ በህዋሓት በኩል ጎላ በሎ ቢታይም በኦሮምያ፤ በአማራ ክልል ባአንዳነድ ቡዱኖችና ገለ ስቦች የሚታየው ዕንቅስቃሴ በሬ ሆይ ሳሩን አየህና ገደሉን ሳታይ የሚያስኝ ነው፤

አሳፋሪው ጉዳይ ደግሞ አንዱ ባንዱ ቤሄር ስም( የራሱን ብሄር እየዘለፈና እያንኳሰሰ መሆኑ ሳይረዳ) ለፓለቲካ ጥቅም ሲባል በሬ ወለደ ፕሮፖጋንዳ መንዛት የሞራል ድቀትን ከማስያቱ በተጨማሪ ከኢትዮጵያዊ ሞራልና ስነ ምግባር ውጭ መሆኑ አለመገንዘብን ያሳያል፤ በርግጥ ሥልጣን ሱስ ነውና ሱስኞቹ ሀይ ልንላቸው ይገባል፤ የነሱን ፈለግ ተከትለን ላም ባልዋልችበት ኩበት ለቀማ የምንሄድ እንሱ ያዘጋጁልን ወጥመድ እይዘቀጥን መሆኑ ልንገነዘብ ይገባል፤

ሁላችንም ልንገነዘብ የሚገባን ነገር ቢኖር ምንም ዓላማ ይኑረን የኢትዮጵያን ሕዝብ በቤሄር ቤሄረስብ ልንለያና ልንበታትነ አቅሙም ሆነ ሞራሉና ስብዕናው የሌለን መሆኑ ነው፤ ብዙዎች ካሁን በፊት ሞኩረውት እንሱ ተንኮታኮቱ እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደንበረው ቀጠል አልተበታትነም ይህም በጥቂቶች መልካም ፈቃድ ሳይሆን በያንዳዱ ቤሄር ቤሄረሰብ ውስጥ ያለው ዘረ መልና ስብዕና የመነጨ ነው፤

ለኢትዮጵያ የቦክር ልጅና የእንጀራ ልጅ የለም ሁላችንም ከየትኛውም ቤሄር ቤሄረስብ እንሆን ለኢትዮጵያ የቦኩር ልጆች እንጂ ማንም የእንጀራ ልጅ የለም፤ የለውጡ አመራርም ቢሆን እስካሁን ያሳየው አካሄድ ይበጅ፤ ይደግ ይመንደግ እንዳስኝ ሁሉ ቀስበቀስ እንደ መንግሥት ሕግና ስርዓት ማስከበር የግድ ይለዋል።

በሕገ መንግስቱ አንቀጸ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 “ ሕገ መንገስቱ የበላይ ሕግ ነው ማንኛውም ልማዳዊ አሠራር እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ ከዚህ ሕገ መንግሥት የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት የለወም” ይልና ቀጥሎም በዚሁ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 እንዲህ ሲል” ማነኛውም ዜጋ፤ የመንግሥት አከላት፤ የፖለቲካ ድርጅቶች ሌሎች ማሕበራት ________ ሕገ መንግሥቱ የማከበርና ለሕገ መንግሥቱ ተገዤ የመሆን ሀላፊነት አለባቸው” ሲል በግልጽ አስፍራል።

ዳር ድንበርን በሚመለከትም እንዲህ ይላል   አንቀጽ 2 “የኢትዮጵያ የግዛት ወሰን የፌደራሉ አባሎች ወሰን የሚያጠቃልል ሆኖ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች የተውስነ ነው” በማለት ካስፈረ በኃላ የፌደራል መንግሥት ይህን ጉዳይ የመከታተል ሥልጣን እንዳለው በማያሻማ ሁኔታ በአንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጸ 1 “የፌደራል መንግሥት ሕገመንግሥቱን ይጠብቃል ይከላከላል” በማለት አስቀምጦታል። ይህም በመሆኑ  በተቀመጠው የሕገ መንግሥቱ ደንጋጌ የኢትዮጵያን ዳር ድንበር የማስከበር ግዴታው ሊወጣ ይገባል፤ በአንድ ሕገ መንግስት በምትመራ ሀገር በፌደራል አወቃቀር ስም ከሕግ በላይ የሚኖርበት አካባቢ ሊኖር መፈቀድ የለበትም፤ ስብዓዊ መብት መከበር የሚጀመረው ሁሉም በሕግ ፊት ዕኩል ሲሆን ነው።

የለውጥ አመራሩ የወደፊት ራዕይ ምንነትና የሚከተለው አካሄድ ለህዝቡ ይፋ በማድረግ ገንፍሎ የተነሳው ህዝባዊ የለውጥ ፍላጎት መልክ ማስያዝ ይጠበቅበታል። የፈለግነው ቦታ ለመድረስና የምንከተለው የጉዞ አቅጣጫ በገሀድ ከታወቀ ህዝባዊ ተሳትፎ ያለው ጉዞ ይሆናል ልማቱም ዕንቅፋቱም የጋራ ስለሚሆን ጣት ከመቀሳሰር ወጥተን ሁሉንም የጋራ ጉድያችንና አብሮነታችን ይለመልማል።

ህዝብን ያቀፈ ህዝብን ያዳመጠ አመርራ ምን ጊዜም ውጤትም ነው። እኔ ስለ አንተ አውቅልህ አለሁ፣ የምልህን ተቀበል ጊዜው አልፎበታል። ምንም እንኳ በመነሻው ሆ ባይ ቢበዛም ያንኑ ሆታ ይዞ መቆየትና መጓዝ ከባድ ነውና፣ምክንያቱም የሰው ፍላጎት ተለዋዋጭና ገደብ የለሽ በመሆኑ በሰከነና በትዕግስት በአንጻራዊ መልኩም ቢሆንም ማስተናገድ ግድ ነው። ለዚህም በግልጽና በህቅ የተመሰረተ አመራር ይጠይቃል ። እንዲህ ከሆነና ለህዝብ እውቅና ከተሰጠ በህዝብ የባለቤትነት ስሜት እየስረጸ ስለሚሄድ የማይሆነውና የሌለው ነገር አይጠይቅም ብቻ ሳይሆን የድርሻውን ለመወጣት ከልብ ይሳተፋል።